SOS CHILDREN'S VILLAGES ETHIOPIA

ኤስ ኦ ኤስ አጸደ ህጻናት ጅማ

**የኤስ ኦ ኤስ አፀደ ህፃናት የወላጅ መተዳደሪያ ደንብ**

የወላጅ/ አሳዳጊ/ ሚና በአፀደ ህፃናት ውስጥ፡-

1. የህፃናትን ንፅህና በተገቢው ሁኔታ መጠበቅ/ ጥፍር መቁረጥ፣ ፓንት ማልበስ፣የፀጉር ንፅህና መጠበቅ/ ወዘተ
2. የፀጉር አቆራረጥና የሴት ህፃናትን የፀጉር አሰራር ስርዓቱን የተከተለ ማድረግ።
3. በየቀኑ ህፃኑን ወደ አፀደ ህፃናት መላክ ህመም ኖሮት ሲቀር ለክፍል መምህርት ደውሎ ማሳወቅ ።
4. የአፀደ ህፃናት የደንብ ልብስ / ዩኒፎርም /አፀደ ህፃናቱ ባስቀመጠው ዓይነት በአግባቡ ማልበስ / ዩኒፎርም ሳትለብስ/ሳይለብስ / የተላከ ህጻን ወደ ቤት ይመለሳል።
5. ወላጅ ስለ ልጁ የመማር-ማስተማር ሂደትም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ለውይይት በሚጠራበት ጊዜ ጥሪን እና ሰዓትን አክብሮ መገኘት።
6. የወላጅ/ አሳዳጊ/ የአፀደ ህፃናት ስብሰባ ተሳትፎ ማድረግ ለህፃኑ ለሚመጣው የትምህርት ሂደት ውጤታማ እና ጥሩ የሆነ እርዳታ ለማድረግ በየጊዜው መምጣትና ውይይት መሳተፍ።
7. ህፃናት ወደ አፀደ ህፃናት ሲላኩ ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑት ቁሳቁሶችን እንደ እርሳስ፣ላፒስ፣ደብተር፣የቀለም እርሳስ፣መለማመጅ መጽሀፍ የመሳሰሉትን ማስያዝ ።
8. እናት ወይም አባት ከህፃኑ ጋር የቀረብ ግንኙነት ስለአለ በየእለቱ ውሎውን መጠየቅና ግንኙነትን ከልጅዎ ጋርማጠናከር።
9. ከክፍል መምህርት ጋር ወላጅ የቀረበ ግንኙነት በማድረግ ስለ ህፃኑ በቅርበት ማወቅና መርዳት አስፈላጊ በሆነበት ሰዓት በመምጣት ውይይት ማድረግ።
10. በደብተርም ሆነ በመለማመጃ መጽሀፍ የሚሰጠውን የቤት ስራ ማሰራትና ለማሰራትዎ ፊርማ ማኖር።
11. ለህጻኑ የተሰጠውን የቤት ሰራ እራሱ እንዲሞክር መንገድ ማሳይት እና በሌላ ወረቀት ማለማመድ ሌላ አካል ጽፎ የሚላክ የቤት ስራ ሰልሚለይ እንዳየሰሩ እናሳስባለን።
12. የቤት ሰራውን መለየት የሚችሉት መምህርቷ ከላይ ባለው ሳጥን ውስጥ ምልክት ስታደርግ መሆኑን ማየት።
13. ህፃናት የተሻለ እድገት እና ውጤት በትምህርት ላይ ለውጥ እንድታምጣ/ እንዲያመጣ/ ወላጅ የእራሱን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል።
14. ህፃናት ወደ አፀደ ህፃናት ሲመጡ ምንም ዓይነት ገንዘብ ለማባበያነት መስጠት የለበትም።
15. የህጻኗን/ የህፃኑን / ቁርስ እና ምሳ መጥኖ ማስያዝ/ ቁርስና የምሳ ሰዓት ተቀራራቢ ስለሆነ/።
16. ሌሎች ህፃናት እንዳይጓጉ ሲባል ጁስ፣ቸኮላት፣ ወተት ወዘተ. የመሳሰሉትን ይዘ አለመምጣት።
17. ልጅዎን ወደ አጸደ ህጻናት በሚልኩበት ጊዜ የኮቪድ -19 ፕሮቶኮል በሟሟላት መላክ። / 2 ማስክ አንዱ ቢቆረጥ ተለዋጭ እንዲኖር ማስያዝ/

እኔ ______________________________ የተማሪ/ ስም/ _________________________ ልጄ
በኤስ ኦ ኤስ አፀደ ህፃናት ገብታ/ ገብቶ/ እንድትማር/ እንዲማር/ ሳደርግ ተማሪዋም/ተማሪው/
የአፀደ ህፃናቱን ደንብ በማክበር እና ከእኔም የሚጠበቀውን አስፈላጊውን ግዴታዎች ሁሉ የምፈፅም መሆኑን እና ሃላፊነት መውሰዴን አረጋግጣለሁ።

ቀን _______________________________

ስልክ ቁጥር ________________________________

የተማሪዋ/ ው/ የክፍል ደረጃ _________________

ፊርማ ____________________________________